# የሕያው ቃል ቤተ ክርስቲያን በኦታዋ
# መሠረታዊ የእምነት አንቀጽ

## መግቢያ

የሕያው ቃል ቤተ ክርስቲያን ተልዕኮዋ እግዚአብሔርን የማያውቁና የማያምኑ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እግዚአብሔርን እንዲያውቁና እንዲያምኑ ወንጌልን መስበክና መኖር እንዲሁም ለማህበረ ምእመ ኗ እግዚአብሔርን በማወቅ መንፈሳውያን ሆነው የሚሠሩበትንና የሚያድጉበትን መንገድ ማመቻቸትና በ መንፈሳዊ ጉዞአቸው መርዳት ነው። ቤተ ክርስቲያን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እውቀት የምታድግ የእግ ዚአብሔር መንፈስና እውነት የሚመራት የአማኞች አካል ስትሆን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረተው ን የእግዚአብሔርን እውነት በማመንና በመከተል ጸንታ ትቆማለች፤ ስለዚህም ይህ መሠረታዊ የእምነት አንቀጽ ለሕያው ቃል ቤተ ክርስቲያን ጅማሪዋ ሲሆን ወደፊት ይህች ቤተ ክርስቲያን በደረሰችበት መረ ዳትና ልምምድ መሠረታዊ የሆነውን የእምነት አቋሟን የሚገልጹትን አሳቦች ሳትለውጥ ይህን የእምነት አንቀጽ እንደገና ልታሻሽል ትችላለች።
(ማቴዎስ 28፥19-20። 2ኛ ጴጥሮስ 3፥18። ዮሐንስ 3፥16)

## 1. ቅዱሳት መጽሐፍት

መጽሐፍ ቅዱስ 39 የብሉይ ኪዳን 27 የአዲስ ኪዳን መጽሐፍትን የያዘ ቅዱስ፣ ሕያውና የእውነት ሁሉ መሠረት መሆኑን፣ እግዚአብሔር ለሰው ደህንነት ይሆን ዘንድ ራሱን በሙላት የገለጠበት፣ በአማኞች ሕይወትና በቤተ ክርስትያን ትምህርትና አሠራር እንዲሁም በነገር ሁሉ ላይ ሙሉ ሥልጣን ያለውና የ ማይሻር፣ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት የተጻፈ እንደሆነ እናምናለን።
(2ኛ ጢሞቴዎስ 3፥15ና17። ዮሐንስ 17፥17። 2ኛ ጴጥሮስ 1፥20,21)

## 2. ቅዱስ ሥላሴ

ሕያውና እውነተኛ በሆነ፣ ቅዱስ፣ አፍቃሪ፣ ዘላለማዊ፤ ያልተወሰነ ኃይልን፣ ጥበብንና መልካምነትን በ ተሞላ፤ የሁሉ ፈጣሪና ሁሉ እንዲኖር በሚያደርግ በአንድ እግዚአብሔር እናምናለን። በዚህ አንድነት ውስጥ በተገለጠ በመለኮት ባህሪው፣ በዘላለማዊነትና በሥልጣን አንድ፣ በአካል ሦስት በሆነ ሕያውና እ ውነተኛ አምላክ በእግዚአብሔር አብ፣ በእግዚአብሔር ወልድ፣ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ እናምናለን።
(ዘፍጥረት 1፥1፣ 17፥1። ዘጸአት 3፥13-15፣ 33፥20። ዘዳግም 6፥4። መዝሙር 90፥2። ኢሳይያስ 40፥28 - 29። ማቴዎስ 3፥16-17፣ 28፥19። ዮሐንስ 1፥1- 2ና4፥24፣ 16፥13፣ 17፥3። ሐዋርያት ሥራ 5፥3-4፣ 17፥24 - 25። እብራውያን 1፥8፣ 1ኛ ዮሐንስ 5፥20)

### 2.1 እግዚአብሔር አብ

ሰማይንና ምድርን፣ በምድርና በጠፈርም ሁሉ ያሉትን የፈጠረ፤ ሁሉንም የሚገዛ፣ እውነተኛ፣ የማይለወጥ፣ መንግሥቱ የማይሻር፣ ሥፍራ የማይወስነው፣ ሁሉን የሚያውቅ ዘላለማዊ አምላክ እንደሆነ እናምናለን።
(ማቴዎስ 28፥19። ማርቆስ 12፥29። ኤፌሶን 4፥6። ቲቶ 2፥11። ዮሐንስ 16፥27። 1ኛ ቆሮንቶስ 8 ፥6)

### 2.2 እግዚአብሔር ወልድ

ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር በእርሱና ለእርሱ ሁሉን የፈጠረበት ከመጀመሪያ በእግዚአብሔ ር ዘንድ የነበረ ቃል ሲሆን በመንፈስ ቅዱስ የተጸነሰ፣ ከድንግል ማርያም የተወለደ፣ ኃጢአት በማያውቀው ሕይወቱ፣ በተአምራቱና በትምህርቱ እግዚአብሔርን ያሳየን፣ ፍጹም ሰውና ፍጹም አምላክ የሆነ አንድያ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ፤ በትንቢትም አዳኝነቱ እንደተነገረ፣ ለሰ ው ልጆች ኃጢያት በመስቀል ላይቤዛ ሆኖ የሞተ፥ የተቀበረ፥ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን በ ሥጋ የተነሳ፥ ወደሰማይ ያረገ አሁን በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ስለ እኛ መካከለኛ ሆኖ የ ሚማልድ፥ የነገሥታት ንጉሥ፡ የጌቶች ጌታ የሆነ፣ መንግሥቱንም በጽድቅና በሰላም ሊያቆም በታላቅ ክብር በግልጽ እየታየ ዳግመኛ የሚመለስ እንደሆነ እናምናለን።
(ዮሐንስ 1፥1። ቆላስይስ 1፥16። 1 ጢሞቴዎስ 3፥16። ዮሐንስ 3፥16። ማቴዎስ 1፥20። ሐዋርያት ሥራ 10፥36። 1 ቆሮንቶስ 15፥34። እብራውያን 7፥25። ራእይ 19፥16)

## 2.3 <u>እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ</u>

*መንፈስ ቅዱስ እንደ ክርስቶስ የተሰፋ ቃል ለቤተ ክርስቲያን የተላከ አጽናኝ፥ የተሐድሶ ምን
ጭ፥ ለወንጌል ሥራ የሚጠቅሙትን የጸጋ ሥጦታዎች ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጥ፥ በአማኞች
ልብ ውስጥ አድሮ ወደ ንስሐ የሚመራና የንስሐ ፍሬና ለውጥ በአማኞች ሕይወት እንዲኖር የ
ሚረዳ፥ በቤተ ክርስትያን ውስጥ ለቅዱሳን አንድነት ምንጭ የሆነ፣ ሰውን ወደ እውነት እየመ
ራ ወደ ደህንነት የሚያደርስ ዓለምንም ስለ ኃጢያትና ስለፍርድም የሚወቅስ በሥላሴ ውስጥ
ሦስተኛው አካል የሆነ አምላክ እንደሆነ እናምናለን።*
(ዮሐንስ 14፥16-17፣23። ሐዋርያት ሥራ 2፥4፣17፣19፣38። ማቴዎስ 28፥19። 1ኛ ጴጥሮስ 1፥2። ቲ
ቶ 3፥5። 1ኛ ቆሮንቶስ 12፥8፣11። ሐዋርያት ሥራ 20፥28 )

## 3. <u>መላእክት</u>

*መላእክት በእግዚአብሔር የተፈጠሩ ቅዱስ የእግዚአብሔር መልእክተኞችና አገልጋዮች እንደሆኑና ክር
ሰቶስም ዳግም ሲመለስ በክብር አጅበውት የሚመጡ ፍጥረታት እንደሆኑ፣ በትዕቢቱ ምክንያት ከእግዚ
አብሔር ህልውና ፊት የወደቀውን ሰይጣንን በአመጹ የተከተሉት አመጸኞች መላእክት ወይም አጋንንቶ
ች ዛሬም እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለውን አላማ እየተቃወሙ እንዳሉ፣ የታመኑት መላእክት ግን
ዛሬም በዙፋኑ ፊት እግዚአብሔርን ማምለካቸውን እንደቀጠሉ እናምናለን።*
(ራእይ 1፥1፣ 22፥6። እብራውያን 1፥14። ማቴዎስ 25፥31)

## 4. <u>ሰይጣን</u>

*ሰይጣን የአመጽና የክፋት ሠራዊት ራስ በመሆን ተከታዮቹን ይዞ የወደቀ ኪሩብ ነው፤ ከእርሱም ጋር የ
ወደቁት ፍጥረታት በምድር የእግዚአብሔርን አላማና የጌታን ምጻት በመቃወም ተግተው ይንቀሳቀሳሉ፤
ሰይጣን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ክፉ፣ አሳች፣ ነፍሰ ገዳይ፣ ሌባ፣ ፈታኝ፣ የወንድሞች ከሳሽ፣ የዚህ አለ
ም ገዥ በመባል ይጠቀሳል፤ እርሱም በሚያደርገው ተጽእኖ የማያምኑትን ሰዎች ልብ በማጨለም ያስታ
ል።*
(ራእይ 12፥9-10። 2ኛ ቆሮንቶስ 4፥4። ዮሐንስ 8፥44። ራእይ 20፥13)

## 5. <u>ሰው</u>

*ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ወንድና ሴት ሆኖ በእግዚአብሔር የተፈጠረ ነው። ሰው ባለመታዘዝ በኃ
ጢአት ምክንያት በመንፈስና በሥጋው ሞትን ያመጣ ሲሆን ነገር ግን ሰው በክርስቶስ ኢየሱስ የአዳኝነ
ት ሥራ ላይ ባለው እምነትና በእግዚአብሔር ጸጋ ከእግዚአብሔር ጋር በመታረቅ ደህንነትን ያገኛል።*
(ዘፍጥረት 1፥26ና28። 2፥7ና22። ሮሜ 5፥9ና21። 6፥23። 1ኛ ጴጥሮስ 1፥3-9)

## 6. <u>ኃጢአት</u>

*ኃጢአት ያለሕግ በመሆንና በራስ ፍላጎት በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ በአመጽ መነሳትና ለእግዚአብሔር
አለመታዘዝ ነው። በአዳምና ሄዋን ምክንያት ኃጢአት ወደ ሰው ዘር ከገባ ጀምሮ ሰው በኃጢአት ቀንበ
ር ሥር ሆኖ ከእግዚአብሔር በመለየት ኖረ፤ ይህም ቀንበር በእግዚአብሔር ጸጋና በክርስቶስ የደህንነት
ሥራ ብቻ የሚሰበር ቀንበር ነው። ስለዚህ ሰው ኃጢአተኛ ስለሆነ እግዚአብሔር በልጁ በኩል ያዘጋጀ
ው ደህንነት ያስፈልገዋል።*
(1ኛ ዮሐንስ 3፥4፣ 5፥17። ሮሜ 1፥20-21። ሮሜ 3፥23-24። ሮሜ 7፥24-25። ማርቆስ 7፥21ና23 ገላትያ 5፥
17ና21)

## 7. <u>ደህንነት</u>

*ደህንነት ከኃጢአት እስራትና ሞት በመውጣት ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ህብረት ማደስ ነው፤
ደህንነት በሥራ ሳይሆን ክርስቶስ ስለ ሰው ልጆች ኃጢአት በመስቀል ላይ በሠራው የደህንነት ሥራ ላ
ይባለ እምነት የሚገኝ ነጻ የሆነ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ነው፤ ይህም የደህንነት ሥራ ክርስቶስ ከሞ
ት በመነሣቱ ተረጋግጧል። ስለዚህ ንስሀ በመግባት በክርስቶስ ያመኑ የተቀበሉትም ሁሉ ከመንፈስ ቅዱ
ስ የተወለዱ፣ የዘላለም ሕይወትወራሾች ይሆናሉ።*
(ሮሜ 6፥18፣22ና23። ሮሜ 8፥21-23። ኤፌሶን 2፥8-9። 1ኛ ጴጥሮስ 1፥4)

8. **ጸጋ**

ጸጋ ሰው በክርስቶስ የተፈጸመውን የደህንነት ሥራ የሚገልጽ ነጻ የሆነ የእግዚአብሔር ሥጦታ ነው፤ አማኝ በክርስቶስ ላይ ባለው እምነትም ሁልጊዜ ከጸጋ በታች ጻድቅ ሆኖ ይኖራል።
(ሮሜ 3፥24። ሮሜ 5፥2፣15፣17ና 21። ኤፌሶን 2፥8-9። ቲቶ 3፥7)

9. **እምነት**

እምነት እግዚአብሔር ጽድቃችን እንደሆነ፣ በሁሉ ቻይነቱ፣ በቸርነቱ፣ በምህረቱና አዳኛችን መሆኑን ማመን ሲሆን በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ በተጻፈው እውነት መሠረት የእግዚአብሔርን ህልውና፥ እግዚአ ብሔርንም ለሚፈልጉት ሽልማት፥ በክርስቶስ ለሆኑትም የዘላለም ሕይወት እንዳላቸው መቀበል ነው።
(እብራውያን 11፥6። ኤፌሶን 2፥8-9። ያእቆብ 2፥17። ሮሜ 6፥23። 10፥17)

10. **ንስሀ**

ንስሀ በመንፈስ ቅዱስ ወቀሳና ምሪት የሚሆን ከኃጢአት ወደ እግዚአብሔር መመለስ ሲሆን፤ ሰው የሕ ይወት አቅጣጫውን ቀይሮ በእግዚአብሔር መንገድ ለመሄድ መወሰኑን የሚያሳይ የአእምሮና የባህሪ ለ ውጥ ነው።
(ሐዋርያት ሥራ 2፥38። ሮሜ 2፥4፣10፥17፣ 12፥2። 2ኛ ጢሞቴዎስ 2፥25። ማቴዎስ 3፥8)

11. **ጽድቅ**

ጽድቅ ክርስቶስን እንደግል አዳኝ በመቀበሉና ክርስቶስ ስለእርሱ ሞቶ ደሙን እንዳፈሰሰለት በማመኑ፣ ንስሀ በመግባትና በደሙ በመታጠብ ምክንያት እግዚአብሔር ምህረቱን ለአማኝ ያሳየበት የምህረት ሥራ ነው።
(ገላትያ 2፥16። ሮሜ 3፥20፣24ና31። 4፥18። 5፥1ና9)

12. **ቅድስና**

መቀደስ የአማኝ የመለወጥ ምልክትና እድገት ሲሆን ይህም በአማኝ ውስጥ ያደረው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ውጤት ወይም የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ነው።
(1ኛ ጴጥሮስ 1፥2። 1ኛ ዮሐንስ 1፥8። 1ኛ ዮሐንስ 3፥6ና9። ገላ 5፥22-23። ሮሜ 5፥1)

13. **የውሃ ጥምቀት**

አማኞች በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም በውሃ ውስጥ በመነከር በሞቱና በትንሣኤው ከክርስቶስ ጋር ህብረት እንዳላቸው የሚያሳዩበትና ለኃጢአት ሞተው በክርስቶስ ለሚገኘው የጽድቅ ኑሮ እንደተነሱ የሚገልጡበት ሥርአት ነው።
(ማቴዎስ 3፣16። ማቴዎስ 28፥19። ማርቆስ 16፥16። ገላትያ 3፥27። ሮሜ 6፥4-5)

14. **በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ**

የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ወይም በመንፈስ ቅዱስ መሞላት አማኝ ራሱን ለመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር በ መስጠት ያለውን ሕይወት የሚለማመድበት ልምምድ ነው። በዚህ ልምምድ አማኝ የበለጠ ወደ ኢየሱ ስክርስቶስ እየቀረበ የሚመጣበትና የጠበቀ ግንኙነትን እየፈጠረ የሚመጣበት፣ ለምስክርነትም ኃይልን የ ሚቀበልበትና በመንፈሳዊ ሕይወቱ የሚያድግበት ልምምድ ነው። አማኞች በትጋት የመንፈስ ቅዱስ ሥ ጦታዎች የሚገኙበትን የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት መፈለግ አለባቸው።
(ማቴዎስ 3፣11። ሐዋርያት ሥራ 1፥5ና8፣ 8፥12-17፣ 10፥44-46። ኤፌሶን 5፥18። ሉቃስ 24፥49)

15. **የጌታ እራት**

የጌታ እራት የክርስቶስን ሥቃይ፥ ሞቱንና ትንሣኤውን ለማሰብ የሚደረግ መታሰቢያ ነው፤ ይህንንም ሥርአት አማኞች ሁሉ ጌታ ዳግም እስኪመጣ ድረስ ይፈጽሙታል።
(ማቴዎስ 16፥24፣ 26፥26-30። 1ኛ ቆሮንቶስ 10፥16-17፣ 11፥23-32፣ 14፥26, ራእይ 3፥20)

16. **<u>ቤተክርስቲያን</u>**

***ቤተክርስቲያን በክርስቶስ በማመን ዳግም የተወለዱና የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሆኑ ምእመናን አንድነ ት ስትሆን በክርስቶስ ሞትና በመንፈስ ቅዱስ መውረድ የተመሰረተች ናት። ቤተ ክርስትያን ወንጌልን የመስበክ፣ የክርስቶስን ትእዛዛት የማስተማርና መንጋዎቹዋን በመመገብ የማሳደግ ኃላፊነት ተሰጥቶአታ ል። በእግዚአብሔርን ቃልና በመንፈስ ቅዱስ በመመራት ተልእኮዋን የምትፈጽም የክርስቶስ አካል ስት ሆን የአካሉ ራስ ክርስቶስ ነው።***

(1ኛ ***ቆሮንቶስ*** 12፡13፣ ***ሮሜ*** 8፡9፣ ***ኤፌሶን*** 1፡22። ***ሐዋርያት ሥራ*** 2፡1ና47 ***ቆላስይስ*** 1፡18። ***ማቴዎስ*** 28፡19 -20)

*ሀ.* ***<u>አለም አቀፍ ቤተክርስቲያን</u>***

***በክርስቶስ ዳግም የተወለደ ሁሉ አለም አቀፍ አካልነት ያላት የሙሽራይቱ የክርስቶስ ቤተክር ስቲያን አባል ነው።***

(***ኤፌሶን*** 5፡25። 1ኛ ***ጢሞቴዎስ*** 3፡15። ***ቆላስይስ*** 1፡18)

***ለ. <u>አጥቢያ ቤተክርስቲያን</u>***

***አጥቢያ ቤተክርስቲያን ከአለም አቀፍ ቤተክርስቲያን ጋር በአንድነት የምትሠራ የክርስቶስ አካ ል ነች፤ አማኞች በተለያየ ስፍራ በአንድነት እግዚአብሔርን የሚያመልኩባት፣ ቅዱስ ምሥጢ ራት የሚካሄዱባት፣ ወንጌል ለሁሉ የሚሰበክባትና በእግዚአብሔር የተመሠረተች አካል ናት።*** ( ***ሐዋርያት ሥራ*** 1፡8፣ 11፡19-24። 2ኛ ***ጢሞቴዎስ*** 2፡2። 1ኛ ***ጴጥሮስ*** 5፡2)

17. **<u>የመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታ</u>**

***አማኞች ቤተክርስቲያንን ለማገልገልና ለማነጽ የእግዚአብሔር ማንነት በቤተክርስቲያንና በውጭ ባሉት ዘንድ እንዲገለጥ ከእግዚአብሔር የሚሰጣቸው መለኮታዊ ኃይልና ልዩ ልዩ ችሎታዎች ናቸው።***

(1ኛ ***ቆሮንቶስ*** 12፡ 4-11። 14፡12, 24-25)

18. **<u>ፈውስ</u>**

***ፈውስ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ለአማኞች ሁሉ የተሰጠ ስልሆነ ቤተክርስቲያን ለታመሙ መጸለይንና ሥጦታውን መለማመድን ቤተክርስቲያን ታበረታታለች።***

(***ማቴዎስ*** 8፡16፣17 ***ያእቆብ*** 5፡14። 1ኛ ***ቆሮንቶስ*** 12፡28-30)

19. **<u>ክርስቲያን</u>**

***ክርስቲያን በክርስቶስ በማመን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሆነ በሕይወቱ ከእግዚአብሔር ጋር በቅድስና ህብረት የሚያደርግና የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሚታይበት ሰው ነው።***

(***ሮሜ*** 8፡9፣14። 1ኛ ***ዮሐንስ*** 2፡4-6። ***ማቴዎስ*** 22፡37-39። ***ዮሐንስ*** 13፡35። ***ገላትያ*** 5፡22-23)

20. **<u>ጋብቻና ቤተሰብ</u>**

***ጋብቻ በእግዚአብሔር የተመሠረተ በወንድና በሴት ጾታዋች መካከል ለእድሜ ልክ በሆነ መንፈሳዊና ስ ሜታዊ አንድነት በሕግ በቤተክርስቲያን የሚረጋገጥ ቅዱስ ሥርአት ነው፤ አማኝ ሊያገባ የሚገባው አማ ኝ የሆነውን ብቻ ሲሆን ነገር ግን ጌታን እንደ ግል አዳኝ አድርጎ ከማመን በፊት የተከናወነውን ጋብቻ በሰላም ሊጸናና ምስክርነት በቤተክርስቲያን ሊሰጥበት ይችላል፤ ጋብቻ ሊፈርስ የሚችለው እንደ መጽ ሐፍ ቅዱስ ቃል መሠረት በዝሙት በፍትወትና በሞት ምክንያት የተረጋገጠ ሲሆን ብቻ ነው።***

( ***ዘፍጥረት*** 1፡27-28፣ 2፡18-24 ***ኢሳይያስ*** 54፡4-8። ***ማቴዎስ*** 19፡4-6። ***ኤርምያስ*** 3፡14)

21. **<u>ፍቺ</u>**

***እግዚአብሔር መፋታትን የሚጠላ ስለሆነ በጋብቻ ውስጥ ይቅርታ መጠየቅና ማድረግ ለፍቺ ትልቅ ፈ ውስ ነው፤ ፍቺ የወንድና የሴት እንዲሁም አንድ የሆነውን ቤተሰብ የሚለያይ በመሆኑ ቤተክርስቲያን እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል መሠረት አጥብቃ ትቃወማለች።***

(***ማቴዎስ*** 19፡8። ***ሚልክያስ*** 2፡16)

22. **ሁለተኛ ጋብቻ**

ሁለተኛ ጋብቻ አስቀድሞ በተጋቡና በመንግሥት ሕግ ጋብቻቸው በተቁዋረጠ አንድ ወንድና ሴት መካከል የሚደረግ ጋብቻ ሲሆን ሁለተኛ ጋብቻ ሊፈጸም የሚችለው እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል መሠረት በሞት ወይም በምንዝርና ኃጢአት ምክንያት የቀደመው ጋብቻ መፍረሱ ሲረጋገጥ ብቻ ነው።

23. **አሥራት**

አሥራት ከአሥር አንድ መስጠትን የምንለማመድበት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተግባር ነው፤ አሥራት መስጠት የብሉይ ኪዳን ሥርአት ሲሆን ቤተክርስቲያን ይህንን ሥጦታ እግዚአብሔር የሰጣትን ተልእኮ ለመፈጸም ለወንጌል መስፋፋት ተግባርና መንጋዎቹዋን ለመመገብ ታውለዋለች፤ አሥራት አማኝ የደህንነትና የመልካም ነገር ሁሉ ምንጭ ለሆነው ለእግዚአብሔር ያለውን ፍቅርና አምልኮ የሚገልጽበት አንዱ መንገድ ነው። (ዘሌዋውያን 27፥30, ማቴዎስ 23፥23 እብራውያን 7፥4, 14 1ኛ ቆሮንቶስ 9፥1,14)

24. **ዳግም ምጽአት**

በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተጻፈው ኢየሱስ ክርስቶስ በኃይልና በክብር ለሁሉ እየታየ ወደዚህ ምድር እንደሚመጣ፣ መንግሥቱንም እንደሚመሠርት እናምናለን።
(ዮሐንስ 14፥3። ራእይ 1፥7፥ 17፥14። ሐዋርያት ሥራ 1፥11። ማቴዎስ 24፥30። 1ኛ ተሰሎንቄ 4፥15-17)

25. **ትንሣኤ ሙታን**

ሙታን እንደሚነሱ ነገር ግን ጻድቃን ለሕይወት ትንሣኤ ኃጥአን ግን ለዘላለም ፍርድ እንደሚነሱ እናምናለን። ለቅዱሳን ትንሣኤ ሙታን ይሆናል ለዚህም እውነት የክርስቶስ አየሱስ ትንሣኤ ለአማኞች ማረጋገጫው እንደሆነና የሚነሣውም መንፈሳዊው አካል መሆኑን እንምንለን፤ ላላመኑት ግን ትንሣኤ ሙታን ከዚህ በኋላ ይሆናል።
(ኢዮብ 19፥25-27። ዳንኤል 12፥2። ማቴዎስ 22፥30-32፣ 28፥1-20)

26. **የመጨረሻው ፍርድ**

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ፈራጅ እንደሆነና ፍርዱም ሁሉን በማወቁና በዘላለማዊው ጽድቅ ላይ የተመሠረተ እንደ ሆነ ይገልጣል። የእግዚአብሔር የመጨረሻው ፍርድ ሰዎች ሁሉ በታላቅ የፍርድ ዙፋኑ ፊት በሚሰበሰቡበት ጊዜ ሲሆን በዚህ ቀን የሕይወት መጽሐፍ ይመረመራል ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን ሽልማትና ቅጣት ይሰጣል።
(መክብብ 12፥14። ማቴዎስ 10፥15፣ 25፣ 31-46። ሉቃስ 11፥31-32። ሐዋርያት ሥራ 10፥42, 17፥31)

## የደቀ መዝሙር ቃል ኪዳን

እግዚአብሔር ለኛ ስለገለጠው ፍቅር ከእኛ ምላሽን ይጠይቃል። ይህ ምላሽ የሚሰጥበት መንገድና ስለዚህም በመጽሐፍ ቅዱስ ከተሰጡት ምሳሌዎች መካከል አንዱ ለሌላው ቃል ኪዳንን ማድረግ ነው። ስለዚህም እያንዳንዱ የቤተ ክርስትያን አካል የሆነ ምእመን በአካሉ የሚገኙትን ወንድሞቹንና እህቶቹን ሊያገለግላቸውና በጸጋና በእግዚአብሔር እውቀት ለሚሆን እድገታችን ያለበትን ኃላፊነት ሊሸከም ቃል ኪዳንንም ሊያደረግ ይገባል። በዚህ ቃል ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔርን በመታዘዝ ለማደግ ራሳችንን ለመስጠት ያለንን ምኞት ስናሳውቅ፣ ለሌሎች ሥጋዊና መንፈሳው ደህንነት ግድ የሚለን እንደሆንንና (ዘፍጥረት 4፥9) ማናችንም ከአዳኛችን ፊታችንን እንዳንመልስ በየጊዜው ልንበረታታ እንደሚጋባ እንገልጻለን (እብራውያን 3፥15)። በሥራና በፍቅርም አንዱ ለሌላው ምሳሌ ሊሆን ይገባል (እብራውያን 10፥24)

## የቃል ኪዳን መሠረት

ይህን የደቀ መዝሙር ቃል ኪዳን የምንገባበት መሠረቱ እንደሚከተለው ነው፦

1. መጽሐፍ ቅዱስ የአዲስና የብሉይ ኪዳንን አጣምሮ የያዘ በሕይወታችን ላይ ሙሉ ሥልጣን ያለው የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ እናምናለን፣
2. ኃጢአተኞች ስለሆንን ደህንነት እንደሚያስፈልገንና በእኛ ሥራ ሳይሆን ክርስቶስ ኢየሱስ በሠራው ሥራ ላይ ያለን እምነት ብቻ ለደህንነታችን በቂ እንደሆነ እናምናለን፣

3. ክርስቶስ ኢየሱስ ሁሉን የሚገዛ የሕይወታችን ጌታ እንደሆነና በእርሱም ጸጋ እርሱን ማገልገልና እ ግዚአብሔርን ደስ ከማያሰኝ ነገር ፊታችንን መልሰን እርሱን ደስ ማሰኘት እንደምንችል እናምናለን ፤

4. የሕያው ቃል በመባል የሚታወቀው ይህ የእግዚአብሔር ጉባኤ በእግዚአብሔር ጸጋ፣ በአዳኛችንና በአምላካችን እውቀት እንድናድግ የሚረዳን ጉባኤ እንደሆነ እናምናለን። ስለዚህም የቤተ ክርስትያ ኒቱን መተዳደሪያ ደንብ በመከተል ለሚሠሩ፣ ለመንፈሳዊ ደህንነታችንም ተግተው ለሚሠሩና ስለ አገልግሎታቸው በእግዚአብሔር ለሚጠየቁ መንፈሳዊ መሪዎች ራሳችንን እናስገዛለን።

## ቃል ኪዳን

ስለዚህ በዚህ መሠረት እንደ ሕያው ቃል ቤተ ክርስትያን በኦታዋ አባል ጌታን በሚያስደስትና ለእርሱ እንደሚገባለመኖር በአንድነት ቃል እንገባለን።

በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ እግዚአብሔርን በእውነትና በመንፈስ በግል፣ በቤተሰብና እንደ ክርስቶስ አካል በአንድነት ልናመልከውና አምልኮአችንን ለመግለጽም በማንኛውም የህይወታችን አቅጣጫ እግዚአብሔ ርን ለመታዘዝ ቃል እንገባለን።

እንዲሁም በግል ሕይወታችን፣ በቤተሰባችንና በየትኛውም በምንገኝበት ቦታ የሕያው የእግዚአብሔርን እውነት ለዓለም ለመመስከር በክርስቶስ የነበረውን ባህሪ በሕይወታችን ለማሳየት ቃል እንገባለን

በሁሉም የሕይወታችን አቅጣጫ ለእግዚአብሔር በመታዘዝ እንድናድግና በእግዚአብሔር ላይ ያለን እም ነት እንዲያድግ ክርስቶስ እኛን እንደተንከባከበን አንዳችን ሌላውን በታማኝነት እያበረታታን፣ በእምነታ ችን እየተደጋገፍንና እርስ በርስ እየተያየን ለመንገዝ ቃል እንገባለን።

ለጌታ ያለንን ፍቅርና ለእርስ በርሳችን ያለንን ታማኝነት ለማሳየት በሥህተት ወይም በኃጢአት የሚገኙ ትን ወንድሞቻችንንና እህቶቻችንን ለማስጠንቀቅና ለመገሰጽ በማቴዎስ 18፥14-17 ላይ የተጠቀሰውን መ መሪያ ለመከተል ቃል እንገባለን።

የእያንዳንዱን አባል ሥጦታ በቤተ ክርስትያናችን ውስጥ ለሚደረገው የእግዚአብሔርን መንግሥት የማ ስፋት ሥራና ቤተ ክርስትያን በንጽህና እያደገች አምልኮን እንድትቀጥል በማድረግ አካሉን ለማሳደግ እንዲውል በማበረታታት ልንጠቀምበት ቃል እንገባለን

ልጆቻችንን በእግዚአብሔር ምክር በመምራት ለማሳደግና እግዚአብሔርን በማወቅ በመንፈሳዊ ሕይወታ ቸው የሚያድጉበትን መንገድ ለማመቻቸትና በምንችለው መንገድ ሁሉ በቤተ ክርስትያናችን ውስጥ ያለ ውን የልጆችን አገልግሎት ለመርዳት ቃል እንገባለን።

በተጨማሪም እግዚአብሔር እንዳበለጸገን የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋት ጊዜአችንን፣ የተፈጥሮ ችሎታችንንና ያለንን ነገር ሁሉ በመጀመሪያ በዚህች በክርስቶስ አካል ላሉትና በአካሉ ላሉት አገልግሎ ቶች፣ ከዚያምበምንኖርበት ከተማና በዓለም ዙሪያ ላሉትና ለተቸገሩ ለመስጠትና ለወንጌል ሥራ በሁሉ ም አቅጣጫ ለመቆም ቃል እንገባለን።

ደካሞች መሆናችንንና የበቃን አለመሆናችንን በመረዳት፣ እንዲሁም በራሳችን ምንም ማድረግ እንደማ ንችል በማወቅ ይህንን ቃል ኪዳን ለመፈጸም ስንሞክር በትህትና ሆነን የእግዚአብሔርን እርዳታና ምሪ ት እንጠይቃለን።